# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 21-12-2012 تاريخ

Lakk.: No.: 20/stm-abo/2012 رقم

## የኦሮሞና ሌሎች ስደተኞችን ያጋጠመውን የባህር ላይ አደጋ በተመለከተ

## የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ከኣንድ መቶ በላይ የሚገመቱ ስደተኞች ከፑንት ላንድ ራስ ገዝ ኣስ ተዳደር ቦሳሶ ወደብ ተነስተው በጀልባ ወደ የመን እየተጉዋዙ ሳለ ባህር ላይ በተከፈተባቸው ተ ኩስ ኣብዛኞቻቸው ሞተዋል። በዚህ የጉዞ መስመር ላይ ስደተኞችን እንዲህ ያለው ኣዳጋ ሲ ያጋጥማቸው ይሂኛው የመጀመሪያ ኣይደለም። ባለፉት ጥቂት ኣመታት ውስጥ በመሰል ኣደጋ ሺዎች በባህር ላይ ሞተው የኣሳ ነባሪ እራት ሆነዋል። ወደ የመን ለመሻገር ሲጥሩ ከሚሞቱት እነዚህ ስደተኞች ኣብዛኛውን ቁጥር የያዙት ደግሞ ኦሮሞዎች ናቸው። በዚህኛው የቅርብ ጊዜ ኣደጋም ከሞቱት ስደተኞች ኣብዛኞቹ የኦሮሞ ሰደተኞች መሆናቸው ተረጋግጧል።

የኦሮሞ ተወላጆች ኣገራቸው ላይ የሚደርስባቸውን የወያኔ መንግስት ወከባ ሽሽት ወደ ጎሮቤት ሃገራት በብዛት ይሰደዳሉ። በጎሮቤቶቹ ኣገራት ውስጥም የወያኔ መንግስት ከሃገራቱ መንግስታት ጋር በመሆን በስደተኛ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ የሚያደርሰው ኣደንና ሰቆቃ የከፋ ስለሆነ ስ ደተኞቹ ባህር ኣቁዋርጠው ወደ ሶስተኛ ኣገር ለመሰደድ ይገደዳሉ። በሃገር ቤትና በጎሮቤት ሃገሮች ውስጥ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ እንዲህ ያለው ዘግናኝ ኣደጋ የሚደርሰው ኦሮሞ የሃገሩ ባለቤት መሆን ባለመቻሉ ነው።

በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) የሃገር ባለቤትነት መብት ተነፍገው ህይወታቸውን ለማትረፍ የሚሰደዱትን ዜጎች ለማስተናገድና ለመርዳት በኣለም ኣቀፍ ደረጃ የተቁዋቁዋመ ተቁዋም ነው። ይሁን እንጂ UNHCR በነዚህ ጎሮቤት ሃገራት ውስጥ ቢሮዎች እያሉት በኦሮሞ ስደተኞች ላይ እንዲህ ያለው ዘግናኝ ኣደጋ በተደጋጋሚ መድረሱ ኣ ሳዛኝ ነው። የስደተኞች ተቁዋሙ በተጣለበት ሃላፊነት መሰረት በባንዲራው ስር ለተጠለሉት እ ነዚህ ስደተኞች ተገቢውን መስተንግዶና እርዳታ ቢያደርግላቸው ኖሮ እንዲህ ያለው ኣደጋ ተደጋግሞ ባልተከሰተ ነበር።

ስለሆነም በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር UNHCR ያለፉትን ድክመቶቹን በማረም በፖለቲካ ኣፈና ምክንያት ከሃገራቸው በገፍ ተሰደው በሶማሊያ፣ ሶማሊ ላንድ፣ ፑንት ላንድ፣ ጅቡቲ፣ የመን፣ ኬንያ እና ሱዳን ውስጥ ለከፍተኛ ሰቆቃ ለተዳረጉት የ ኦሮሞ ስደተኞች ተገቢውን ኣያያዝ በማድረግ የቆመለትን ኣላማ እንዲያረጋግጥ ማስታወስ እንወዳለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ታህሳስ 21, 2012

P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea |Tel 2911 153848 | *www.oromoliberationfront.org*